**ፍትህን ፍለጋ፡ ዳኝነት አሰሳ**

**የአባኪያ ማስታወሻ፤ አባኪያ ተመልሷል፡****

**ትናንት ለጠበቆቻችን፡ ዛሬ ደግሞ ለዳኞቻችን፡**

**"ፍትህን ፍለጋ፡ ፍትህን አሰሳ"**

"ፍትህን ፍለጋ፡ ፍትህን አሰሳ" የሚቀጥለው የቴዲ አፍሮ ዘፈን አልበም መጠሪያ ይመስለኛል። "ቃሊቲ ቃሊቲ" ሊለውም ይችላል። መቼም ዶ/ር ብርሀኑ ወይም ኢንጂነር ሀይሉ ወይንም ብርቱካን ሚደቅሳ ቢዘፍኑ አያምርባቸውም። ነገር ሁሉ ለበጎ ነው የሚለውን የሀዋርያውን ቃል ካመንበት፡ ምናልባትም የቴዲ አፍሮ መታሰር ለበጎ ነው። ከዚህ ቀደም ጽሁፌን ያቆምኩበትን አልዘነጋሁም። ወደዚያ እመለሳለሁ። ለጊዜው ግን ፈተና ላይ ከርሜ ጠፋሁኝ። ኢትዮጵያ የተውኩትን/ያቋረጥኩትን ትምህርት እዚህ ቀጥያለሁ። ይሄ የጀመርኩትን ትምህርት፡ ምእራብና ምስራቅ ጫፍ ካላቸው፡ ከምእራብ ጫፍ ምስራቅ ጫፍ የመሄድ ያህል ዞሬ ነው የጀመርኩት። መቶ ሰማኒያ ዲግሪ መዞር የሚሉት አይነት ነገር። ቀድሞ እማር የነበረው የcivil law ስርአትን መሰረት ያደረገውን የኢትዮጵያን ህግ ነበር። አሁን ወደ common law ዞሬያለሁ። ህግን፡ ህግ ከሚከበርበት ሀገር ስትማሩት እንዴት ደስ ይላል መሰላችሁ። አሁን የምማረው፡ በተለይ እንግሊዝ፡ ካናዳ፡ አውስትራሊያ፡ አሜሪካና ካናዳ የሚከተሉት የህግ ስርአት፡ ቀደም ሲል፡ ምናልባትም ከአንድ ሺህ ዓመታትም በፊት ጀምሮ የተወሰኑ ውሳኔዎችን መሰረት ያደረጉ፡ መርሆዎችና ህግጋት በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ለሚፈጠርና ለሚገኝ ጉዳይ በተመሳሳይ መልኩ የሚወሰኑበት የህግ ስርአት ነው።

ካናዳ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነበረች። ማለቴ፡ ካናዳን የሰራቻት እንግሊዝ ነች። በግልጽ በህግ እስካልተቀየሩ ድረስ፡ እንግሊዝ የምትከተላቸው የcommon law ህግጋት በሙሉ ካናዳ ውስጥ ይሰራሉ። ያ ማለትም፡ ካናዳ ራሷን ችላ መንግስት የሆነችው ገና በቅርቡ ቢሆንም፡ ከእንግሊዝ ጋር ባላት ትስስር የተነሳ፡ የካናዳ የህግ ስርአት ብዙ መቶ አመታትን ወደኋላ ይጓዛል። የሆነ ሆኖ፡ ለዛሬው ጽሁፌ ያንን ሁሉ በማተት ጊዜ ሳላባክንባችሁና፡ ገና አንደኛ አመቴን መጨረሴ መሆኑን እየጠቆምኳችሁ ብዙ ዝርዝር ሳትጠብቁ ወደአንድ ከካናዳ የህግ ስርአት ያደነቅኩትና፡ የቀናሁበት ህግ ትምህርት ቤትም ሳትገቡ፡ የምትረዱት ነገር እነሆ። የካናዳዊያን የፍትህ ስርአት፡ ህዝቡም በፍትህ ስርአቱ ላይ ያለው እምነት፡ የካናዳዊያን የዳኝነትን ነጻነት ትንሽ አጋንኘው በሰማይ ብቻ ያለ ዳኝነት ይመስላል። ባለፈው ሰሞን እኝ አካባቢ የመጣውን ያንዱን ፍርድቤት ፕሬዚዳንት ጨምሮ፡ ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ፍርድቤት ባለሚሎች በተለያየ አጋጣሚ ወደ ውጭ አገር እየወጡ ያደጉት አገራትን የዳኝነት ስርአት ለመመልከት እድል አግኝተው ሳለ፡ ለምን በመንፈሳዊ ቅናት የአገራቸው ዳኝነት እንደነዚያ ያደጉ አገሮች ባይሆንም፡ በትንሽ በትንሹ እንኳዋን ነጻ እንዲሆን እንደማይጥሩ፡ አይገለጥልኝም። እነሆ ዝርዝር፡ ለኢትዮጵያና ለኢህአዴግ ዳኞች።

**ትናንት ለጠበቆቻችን፡ ዛሬ ደግሞ ለዳኞቻችን፡**

ከዚህ ቀደም ለኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች በነቂስ ጽፌ ነበር። አሁን ደግሞ፡ ትንሽ ጠበብ አድርጌ ለኢትዮጵያ ዳኞች መጻፍ ሻትኩ። ማለቴ፡ ተገደድኩ። እንደችግር መጻፍ የሚቀል ነገር እንደሌለ ተናግሬ ነበር ባለፈው። እንደፍትህ ማጣት የሚያቃጥል ነገር ደግሞ የለም። ፍትህ ከፍትህ መቅደስ ወጥታ፡ ከግለሰቦች ጉንቻ ላይ ስትከፈስ፡ ከግለሰቦች ኪስ ውስጥ ስትዝናናና፡ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እየመነዘሩ ሲከብሩባት፡ ከፊታችን ሲፈጠፍጧት እንደማየት የሚያቃጥል ነገር የለም። ሰው ካንተ የበለጠ ሀይልና ጠብመንጃ ስላለው ብቻ ያሻውን ሲያደርግ፡ የፈለገውን ሲናገርና ሲተፋብህ፡ መለስ ብለህ ፍትህና ፍርድ የምትጠይቅበት ስታጣ፡ ይባስ ብሎም ፍትህን ይሰጡ፤ ፍትህንም ያሰፉ ዘንድ የታጨ ዳኞች፡ ፍትህን ሲያሸመደምዱ እንደማየት የሚያስለቅስ ምን ነገር? ለነገሩ ያሳሰበኝ ያቃጠለኝም ይሄ ግለሰቦች ወይም አምባገነኖች ድንገት በየመንገዱ ፍትህን ወደራሳቸው እጅ ወስደው የሚተረክኩት ነገር አይደለም። ይሄ ፍትህ ይገኝበታል ተብሎ፡ ተለፍቶ ተንከራቶ የሚታጣው የሚዛባው ፍትህ ነው። ፍትህን በትንሽ በትንሹ ከካናዳ እስከ አራዳ እንዳስሳለን። ማለቴ እስከልደታ፡፡ ከስዬ አብርሀ እስከ ቴዲ አፍሮ መሆኑ ነው።

የቴዎድሮስ ጉዳይ በራሱ ላያስደንቅ፡ ላይበርድ ላይሞቅ ይችላል። ነገር ግን በቴዎድሮስ የደረሰ በሌሎች ፍትህ አጥተው በሚጉላሉ ሰዎች የሚደርሰው ፍትህ እጦት ምሳሌ ነው። ባለፈው ሳምንት እዚህ እከተማችን ዶ/ር ብርሀኑ ነጋን ንግግር እንዲያደርግ ጋብዘነው፡ ስለቴዲ አፍሮ መታሰር ተጠይቆ፡ እስሩ ፍትሀዊ አለመሆኑንና ገና ጥፋተኛ ይሁን አይሁን ባልታወቀበትና ባልተረጋገጠበት ሁኔታ እንዲሁም፡ ቢሆንም እንኳዋን በአደጋ እንጂ ሆን ብሎ የሰው ሕይወት ባላጠፋበት ሁኔታ ይሄ እድሜ ልኩን ስለፍቅርና ስለአገር

በመዝፈን የሚታወቅ ዘፋኝ፡ ነጻነቱን መገፈፉ፡ የዋስ መብት መከልከሉም አግባብ እንዳልሆነ ተናግሯል። የቴዲ አፍሮ ጠበቃና ቤተሰቦቹ፡ እሰሩ ፖለተከዊ ትርጓሜ እንዳይሰጠው ይማጸናሉ። የሆነ ሆኖ እነሱ ወደዱም ጠሉም፡ ሁለችንም፡ የሱን እሰራትና የዋስ መብት መነፈግ እንደፍትህ ስርአቱ አንድ መለኪያ ምሳሌ አድርገን ከመውሰድ እንመለስም። በየወረዳው በየቀበሌው ተመሳሳይ እጣ የሚደርሳቸውን እተዘዋወርን መመዝገብ በማንችልበት በዚህ ዝግ ስርአት ውስጥ፡ ቴዲና ቤተሰበቹ ተቀበሉትም አልተቀበሉትም፡ የሱን ጉዳይ ተንተርሰን፡ የፍትህ ስርአተችንን ከመገምገምና ከመተንተን አነመለሰም።እንደው ወቅታዊ ምሳሌ ያህል እንጂ፡ ብዙ መሰል ጉዳዮችን መጥቀስ እንችላለን። ከነእስክንድር ነጋ እስከ ነጻነት ደምሴ፡ ኩ እስከ ፐ መጻፍና ማተት እንችላለን።

**እንደመነሻ፡ መነሻን ማወቅ ጥሩ ነውና**

ሁለት መነሻዎች አሉኝ። አንዱ በቴዲ አፍሮ እየደረሰ ያለው፡ ወይንም ካለፈውና ካየነው ተነስተን ሊደርስበት ይችላል ብለን የገመትነው። ሌላወ በዶ/ር ያእቆብ የተጻፈ ቁጭት። ዶ/ር ያእቆብ ባቀረቡት ጽሁፍ ላይ፡ በኢትዮጵያ ቀደም ሲል ለፍትህና ህግ የነበረው ክብር ከፍተኛ ሲሆን የዳኝነት ስራ ደግሞ በጣም የተለየና እጅግ በጣም የተከበረ ከመሆኑ የተነሳ፡ ለዳኞች የነበረው አመለካከትም የተለየና እነሱን ከፍጡራን ከፍ የሚያደርግ ነበር ብለዋል። ቀጥለውም በጽሁፋቸው፡ የዳኝነት ሥራ እንደ መንፈሣዊ ተግባር ተቆጥሮ ከዳኛው ነፍስ ጋር ትስስር እንደነበረው ከመታመኑ የተነሳ፡ ፍርደ ገምድል ዳኛ በቀጥታ ወደ ገሃነም እንደሚወርድም ይታመን ነበር። ያሁሉ ግን ጥንት ነው። ዛሬ ዛሬ ግን ይላሉ፡ ዶ/ር ያእቆብ፡ “በአገራችን የፍትህ ሥርዓቱ ተሰብሯል ማለት ይቻላል። ለሕግ የነበረው ከበሬታ እየተሸረሸረ፣ ሕጉ ነፃነቱን ተገፍፎ፣ በፖለቲካ ተቀፍድዶ ህዝቡ ለፍትህ ያለው እምነት እየተሟጠጠ ነው።” እነሆ የሰው ልጅ በፍትህ ላይ ያለው እምነት የተሸረሸረ እለት እናንተ በዳኝነት ምግባር ላይ የተቀመጣችሁ ሰዎች ሁሉ ተጠንቀቁ። እንደ ፍትህ ስርአት መሰበር የሰውን ልጅ ቅስም የሚሰብር ነገር የለም። የፍትህ ስርአት ከተሰበረ፡ ምርጫው ምርጫ አይሆንም፡ ንግዱ ንግድ አይሆንም፡ ፍርዱ ፍርድ አይደለም፡ ስልጣኔው ስልጣኔ አይሆንም፡ እምነቱ ሁሉ እምነት አይደለም።

በቀድሞው መንግስት ባለስልጣናት ላይ የደረሰውን እንመልከት። የዛሬ ስንት አመት አካባቢ፡ አስር ዓመት ከታሰሩ በኋላ ነጻ ናችሁ ተብለው የተለቀቁ ባለስልጣናትን በሬድዮ ሰምቻለሁ። ከተፈረደባቸው አመታት በላይም የታሰሩ ሰዎችን ጉዳይ ሰምቻለሁ። ሰው ያለፍትህ አስራአምስት አመት ሲታሰር፡ ካስራአምስት በኋላ ነጻ ነህ ሲባል፡ በእውኑ ነጻ ነውን። የኢትዮጵያ የፍትህ ስርአት እንደዚህ ነው። ስለዚህስ ማን ያውቃል፡ ቴዎድሮስም አምስት ስድስት ዓመት ታስሮ ተጻ ነህ ተብሎ ቢለቀቅ፡ በእውኑ ነጻ ነውን። ይሄ የዳኝነትን ነጻነት የሚፈትሽ ጽሁፍ ያተኮረው፡ በተለይ በፖለቲካዊ ምክንያቶች በሚታሰሩና፡ ከፍርድ ቤቶች ፍትህን በተነፈጉ፡ ጉደዮችና ባለጉዳዮች ላይ ነው። ቴዎድሮስ ካሳሁን ለምን ታሰረ ሳይሆን፡ በዘዚ ገጉዳ ሰስ ከተነሰሳበ ከዛሬ ዓመት ከምናምን ገደማ ጀምሮ፡ በሀምሳ ሺህ ብር ዋስ ተለቆ ሲገባ ሲወጣ እተመለከትነውና፡ የፍትህ ስርአቱን ጥሎ፡ አምልጦ ሊሄድ እንደሚችል አቃቤ ህጉ ባላስረዳበት፡ ፍርድ ቤቱም አቃቤ ህጉን ባላፋጠጠበት ሁኔታ፡ ለምን የዋስትና መብት ተከለከለ ነው። ተከትሎም፡ ሌሎች ደሀ ኢትዮጵያዊያንም ተመሳሳይ እጣ ይደርሳቸው ይሆንን የሚለው ጥያቄ መጣብን።

**ፍትህ በካናዳ እና ፍትህ በኢትዮጵያ፡ ስለሰው መብት መጠበቅ**

ማንኛውም በካናዳ የሚኖር ሰው መብቱ በህግ የተጠበቀና፡ ያለህግ መብቱ ሊገፈፍ የማይችል መሆኑን ያረጋግጣል፡ የካናዳ ህገ መንግስት አንድ አካል የሆነው የካናዳ መብቶችና ነጻነቶች ሰነድ፡ አንቀጽ አንድ። ሆን ብሎ የተደረገ ይሁን አጋጣሚ፡ ካናዳም ኢትዮጵያም/ኢህአዴግ አሁን በሚመሩበት ህገመንግስታቸው ውስጥ፤ የሰውን ልጅ መብቶች የሚያስጠብቁ ተመሳሳይ አንቀጾች አላቸው። ከህገዊ ነጻነት ገር በተያየዘ፡ ሰው ነጻነቱ ቀድሞውንም በሰውነቱ ብቻ የተረጋገጠ ነውና ነጻነቱን ሊያረጋግጥ እስር ቤት ሊከርም አይገባም ነው ነገሩ። የኢህአዴግ ህገ መንግስት ብቻ ሳይሆን፡ ኢሕአዴግ ህገ መንግስቱን የቀዳባቸው አገራት ድንጋጌ እንደዚያ ነው። የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ያላልኩት የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ስለመሆኑ ስላለመሆኑ አስቤ አይደለም። የራሱን የኢህአዴግን ቋንቋ ለመጠቀም ነው። የደርግ ህገ መንግስት የኢትዮጵያ ካልሆነ፡ የኢህአዴግን ህገ መንግሰት የኢህአዴግ ብንለው ኢህአዴግን ራሱን አይከፋውም ብዬ አስቤ እንጂ። የሰውን ልጅ መብት ስለመጠበቅ ሳስብ፡ በህይወቴ ሁሌም ከማይረሱኝና አሁንም ድረስ ተፎካካሪ ያላገኘሁላቸው ፕሮፌሰር አንድርያስ እሸቴ ስለ ሞት ቅጣት ካስተማሩኝ ነገሮች ውስጥ ትዝ የሚለኝ፡ የሞት ቅጣት ተከራካሪዎች/ተቃዋሚዎች ከሚያቀርቡት ተቃውሞ ውስጥ ዋነኛው ተቃውሟቸው፡ የሞት ፍርድ irreversible መሆን ነው። በሞት የተቀጣን ሰው፡ ጥፋቱ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በምን እንመልሰዋል? አስራ አምስት ዓመት ታስሮ ምንም ጥፋት ያልተገኘበትን ሰውስ በምን እንክሰዋለን? ለዚያውም በኢትዮጵያ።

በተለይ እንደኢትዮጵያ ባለች ጠንካራ የፍትህ ስርአትና የወንጀል ምርመራ ልምድ በሌለባት አገር፡ ፍትህን በጊዜና ባግባቡ አለማግኘት ውጤቱ ልክ የለውም። ቤተሰብ ይበተናል፡ ልጆች ይበተናሉ፡ አስራ አምስት አመቱ ብቻ ሳይሆን መጪው ህይወትም ይበላሻል። ወደእስር ቤት መመለሱ ሳይቀል አይቀርም። ሶስት ዓመት በሶርያ እስር ቤት የማቀቀው ካናዳዊ ማህር አራርም ያለው ይኸንኑ ነው። ከመስከረም አንዱ የኒውዮርክ መንታ ህንጻዎች ውድመት በኋላ የአሜሪካ መንግስት የተጠራጠራቸውን አረብ እስላሞች ሁሉ በገፍ ያስር ነበርና፡ ይሄ የሶርያ ተወላጅ የሆነ በዜግነቱ ግን ካናዳዊው ኢንጂነር ማህር አራር ኒው ዮርክ አውሮፕላን ማረፊያ ላይ ከካናዳ መንግስት ፖሊስ ሀይል በደረሳቸው ጥቆማ ይታሰርና፡ መርምረው ምንም ሲያጠቡት፡ ወደካናዳ ከመመለስ ይልቅ ወደ ሶሪያ ይሰዱታል። በሱዳኖች በኢህአዴግ የሚፈለጉን ግለሰብ አንገት ይዞ ወደአዲስ አበባ እንደመወርወር ቁጠሩት። ከስንት ትግል በኋላ ከሶሪያ ተለቆ ሲመጣ፡ በብዙ ጉትጎታ መርማሪ ኮምሽን ይቋቋምና የካናዳ ፖሊስ ባለስልጣናት የተሳሳተ መረጃ ለኤፍ ቢ አይ አሳልፈው በመስጠታቸው፡ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው፡ የጠበቆቹን ዋጋ ሳይጨምር፡ አስር ሚሊዮን ዶላር ካሳ እንዲከፈለው ይወሰናል። ያ ጥሩ ቢዝነስ የነበረው ኢንጂነር ማሃር አራር ግን ያጣሁትን ነጻነትና መልካም ዝና ምንም ገንዘብ አይተካውም ነው ያለው። በነገራችን ላይ ይሄንኑ ተከትሎ የካናዳው ፖሊስ ኮሚሽነር ስልጣኑን ለቋልም። የመርማሪውን ኮሚሽን የመሩት የቀድሞ ዳኞችና ጠበቆች ናቸው። ከምረጫ 97 በኋላ በአትዮጵያ የደረሰውን አፈናና ግድያ እንዲመረምር እንደተቋቋመው ኮሚሽን መሆኑ ነው። ይሄ እዚህ የተለመደ አሰራር ነው። እዚህ ግን የምረ ነው። የኮሚሽኑ ምርመራ ውጤት ያለአንዳች ማሻሻያ ተቀባይነት ያገኛል። ዳኛ እዚህ አገር፡ የቀድሞውም ያሁኑም፡ የፍትህ ቋት ናቸው ተብሎ በሰፊው ይታመናል።

**ወደፍርድ ቤት ስንመለስ፡ ዳኞችም ይቁረጡ፡ ልክ እንደካናዳ**

የፍርድ ቤቶች ዋነኛ ሚና ህግን መተርጎምና የመንግስትን ቅጥ ያጣ ያልተገደበ ስራ መቆጣጠር/መገደብ ነው። ስልጣን ካልተገደበ ያባልጋል። አሁን ባለጌዎቹንና ባለጊዜዎቹን እነደሚያባልገው ማለት ነው። የሆኖ ሆኖ ትኩረቴን የማደርገው በእኩያና አንጋፋ ዳኞች ላይ ነው። መቼም ሰው እያወቀ ሲመጣ፡ በአካባቢው ተሸንፎ፡ አንድም ስጋው ያለዚያም ውጪያዊ ጫና አስጨንቆት ፍትህን ሊያዛባ ይችል እንደሆን እንጂ፡ ማንም ከመነሻው መልካም ዳኝነትን አይወድም ብለን ለመናገር አንደፍርም። ገንዘብና ፍትወት ወይንም የግል ስሜት አንበርክኮት ፍትህን የሚያዛባ፡ እሱ ከዚህ ጽሁፍ ወሰን ውጪ ነው። የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ከመንግስት ሊመጣ በሚችለው ፖለቲካዊ ጫና ምክንያት አንድም ፈርቶ፡ አልያም ስልጣን ፈልጎ፡ ወይንም በጥቅም ተደልሎ ፍትህን ሊያዛባ ስለሚችለው ስጋ ለበስ ዳኛ ነው። ፍትህን ስለማጣት የሚጠየቀው፡ ወይንም ፍትህን ሊያመጣ የሚችለው መንግስት ብቻ አይደለም። ግለሰብ ዳኞችም ቆራጥ መሆን አለባቸው። ዳኝነት አለአድልዎና ያለወገንተኝነት፡ ፍትህን ለማገልገል ምለንንና ተገዝተን የምንገባበት ሙያ እንደመሆኑ መጠን፡ ምንም እንኩዋን ገዢው ፓርቲ በራሱ ርእዮተ አለም የተጠረበ የዳኝነት ፍልስፍና ሊጭንብን ቢጥርም፡ እኛ ግን ዘወትር ያመንበትንና የማልንበትን ፍትህ ከመስጠት ወደ ኋላ ማለት የለብንም።

ፍትህ በካናዳ እንደዚያ ነው። በተለይ ሰው ነጻነቱንና ሰብእናውን የሰውነት ክብሩን የሚነካ ቅጣት የሚያስከትሉ ክሶች ላይ ሁሉ መንግስት የተከሳሾችን መብት እንዲያስጠብቅ ህግም ፍርድቤቱም ያዛል። ጠበቃ ማቆም ብቻ አይደለም። አቃቤ ህግ ክሱን ፍጹም እንዲያረጋግጥ ይገደዳል። እንዲህ ዝም ብሎ ያለአግባብ አግበስብሶ ፍርድ ቤት ማጎር የለም። በዚህ ረገድ የካናዳም የኢህአዴግም/የኢትዮጵያም ህገ መንግስታት የሚሉት አንድ ነው። ለምሳሌ ስለተከሰሱ ሰዎች መብት የሚናገረው የኢህአዴግ ህገ መንግስት አንቀጽ 20፡ በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ባፋጣኝ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ፡ እስኪፈረድባቸውም ድረስ ንጹህ እንደሆኑ እንዲታሰብ፡ አግባብ ባለው ፍረድ ቤት ጉዳያቸው እንዲታይ፡ እንዲሁም ራሳቸውን እንዲከላለኩሉ፡ የአቃቤ ህግ ምስክሮችንም አገላብጠው እንዲፈትሹ፡ በማናቸውም ህጋዊ መንገድ ራሳቸውን ሊከላከሉ የሚችሉበት እድል ካለ፡ ያን እድል እንዲጠቀሙ ስለማስቻል ይደነግጋል። ካናዳም ከዚህ የተለየ ወይም የበለጠ መብት በህገ መንግስቷ አላስቀመጠችም። በካናዳ፡ በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ያላቸው መብቶች በኢህአዴግ ህገ መንግስት ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ልዩነቱ፡ በካናዳ፡ ፍርድ ቤቶቹና ዳኞቹ እንዚህን ህገ መንግስታዊ መብቶች ነፍስ ሲዘሩባቸው፡ በየእለቱ ሊያስጠብቁ ሲተጉ ስናይ፡ በኢትዮጵያ ግን መብቶቹ ባብዛኛው ገና ጥሬና በትላልቅ ፖለተካዊ ክሶች እንዳየነው፡ ዳኞቻችን በቁርጥ የሚያልፏቸው ናቸው። መቼም ይሄንን ለማለት ባለፉት አስራ ሰባት ዓመታት የተፈረዱ ፍርዶችን ሁሉ አገላብጬ ማየት አይገባኝም። አንድ ሰው በፖለቲካዊ ክስ ምክንያት ታስሮ ለአስራ አምስት ዓመት ፍርድ ካላገኘ፡ ያ የፍትህ ስርአት ዶ/ር ያእቆብ እነዳሉት ሰባራ ነው። የፍርድ ስርአት ደግሞ የሚሰበረው በመንግስት ብቻ ሳይሆን መንግስትን በሚያግዙት ዳኞችም ነው። በነፕሮፌሰር መስፍን በነዶ/ር ብርሀኑ የደረሰውን ስንመለከት፡ በቴወድሮስም ይሄ እንደማይደርስ ምንም ዋስትና የለም።

**ወደ ቴዲ ስንመለስ፡ ገንዘቡን ማሰር ሲቻል እሱን ለምን?**

ቴዎድሮስ ካሳሁን ታዋቂ ዘፋኝ ስለሆነ ለሱ ሲባል የሚቀለበስ ህግ አይኖርም። ግን ደግሞ እስኪፈረድበት ድረስም ንጹህ ስለሆነ በተቀነባበረ ክስ ወህኒ መውረድና መታጎር የለበትም። ነጻነት በገንዘብ ሁሉ አይተካም። የቴዎድሮስ ነጻነት በቴዎድሮስ ገንዘብ ሁሉ አይተካም። ነጻነቱን ካጣ ገንዘቡንም ራሱንም ያጣል። ገንዘቡን ቢያጣ ግን ራሱን ካላጣ ይተካዋል። ዳኞች ሆይ፡ በተለይ እንደኢትዮጵያ ባለች፡ የዳኝነት ስርአቱ ከፖለቲካ ወገንተኝነትና ጫና ነጻ ስለመሆኑ አከራካሪ (በግሌ አከራካሪ ሳይሆን ዳኝነቱ በሙሉ ከኢህአዴግ ቁጥጥር የወጣ ነው ብዬ አላምንም) በሆነበት አገር፡ ዳኞች ነጻ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በርግጥም ትልቁና ዋነኛው የፍትሕ መሰረትም በመሆኑ ጭምር፡ አቃቤ ህግ ላይ ማነቆውን ጠበቅ ማድረግ አለባችሁ። ልብ እንበል ህገመንግስታዊ ዋስትና ያስፈለገበት ምክንያት መንግስት ወይም የመንግስት ባለስልጣናት እንዳሻቸው ብድግ እያሉ ኢፍትሀዊ የሆነና ጥንቃቄ የጎደለው እርምጃ እንዳይወስዱ፤ ይሄ ቢከሰት ግን የፍርድ ቤቱም ሚና የነሱን እርምጃ መግራት ነው። ያልተገራ መንግስትና ያልተገራ ፈረስ አንድ ናቸው፡ ሁለቱም ይረጋግጣሉ። ገደል ይከታሉ። ዳኞች ሁልግዜም፡ በተለይም ከሰው ልጅ መሰረታዊ መብትና ነጻነት ጋር በተያያዘ፡ የመንግስትን እርምጃ በጥርጣሬና በጥንቃቄ ማየት አለባቸው። መንግስት የሚወስደው እርምጃ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ያለበት እሱ ራሱ ነው። እንጂ ዳኞች የመንግስት እርምጃ ትክክል ነው፡ የሚቃወም ካለ እሱ ያረጋግጥ ብለው መነሳት የለባቸውም። ለምሳሌ የቴዎድሮስ መታሰርን አስፈላጊነት ማረጋገጥ፡ በእስር ካልቆየም ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ማሳየት ያለበት ራሱ አቃቤ ህግ እንጂ፡ ገና ለገና ዋስትና ሊያስከለክል የሚችል አንቀጽ ስለጠቀሰ ብቻ፡ አንቀጹን እንደወረደ መተግበር ትክክል አይደለም። ለዚያ ለዚያማ ፍርድ ቤትም ባላስፈለገ ነበር።

የዛሬ ስንት አመት አካባቢ አቶ መለስ ዳኞችን ሰብስበው ስለህግ አተረጓጓም ማብራሪያ ሰጡ የሚል ዜና አንብቤ ነበር። በዚህ በካናዳ ህገ መንግስትና ዳኝነት ታሪክ ውሰት ግን፤ በመሰረቱ ዳኞችና ስራአስፈጻሚው ወይንም ህግ አውጪው፡ ሊነጋገሩ የሚችሉት በአዋጅ ብቻ ነው። ህግ አውጪው ህግ አውጥቶ ህጉን በዳኞች ዘንድ እንዲደርስ ካደረገ በኋላ፡ ስለአተረጓጎም ሌላ ስብሰባና ሌክቸር መስጠት ጣልቃ የመግባት ያህል ነው። ዳኞች ህጉን እንዴት መተርጎም እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይምን ስራአስፈጻሚው ማብራሪያ፣ መመሪያ ወይንም መግለጫ ከሰጣቸውማ መጀመሪያውንም ዳኝነቱን የፍትህ ሚኒስቴር ቅርንጫፍ ማድረግ ነው እንጂ፡ ነፃ ፍርድ ቤት ማቋቋም የሚባል ነገርም ባላስፈለገ። በመሰረቱ የኢትዮጵያ ህገመንግስትና የካናዳ ህገመንግስት የሰውን ልጅ መብት ከማስጠበቅ አናጻር ያላቸው፡ አቀራረብ ብዙ የተራራቀ እንደልሆነ ከለይ ጠቅሳለሁ።

## እኛና እነሱ እንደገና፤ ልዩነታችን የትየለሌ

የሰውን ልጅ መብት ከማስከበር አንጻር የኛን አይነቱን ስርአት የሚከተሉ ሀገሮችም ይሁኑ የእንግሊዝና አሜሪካንን ስርአት የሚከተሉ አገሮች ያላቸው ልዩነት ብዙ አይደለም። ሁለቱም ስርአቶች ለምሳሌ የሰው ልጅ ያለአግባብ መታሰር እንደሌለበትና ነጻ ፍርድ ቤት ጥፋተኝነቱን እስኪወስን ድረስ ንጽህናው የተረጋገጠ እንደሆነ ያምናሉ። ልዩነቱ እኛ ይሄንን ህግ የሚያስፈጽም ነጻ ፍርድ ቤት የለንም፡ እነሱ ነጻ ፍርድቤትና በጭንቅላታቸው የሚመራ ዳኞች አላቸው። ዋናው ነጥቤ፡ መንግስት ነጻ ፍርድ ቤት እንዳይኖር የቻለውን ሁሉ ቢያደርግም፡ የግለሰብ ዳኞች ሚናም ወሳኝነት አለው ለማለት ነው። ግለሰብ ዳኞች፡ በህሊናዬ ተመርቼ ይሄንን ብወስን ከስራዩ እባረራለሁ፡ ብለው ከፈሩና የግለሰቦችን መብት ለማስከበር ብቻ ሳይሆን የዳኝነትንም ቅድስና ለማስጠበቅ ደፋር ካልሆኑ፡ ከፈሩና ከተንጸረጸሩ፡ መንግስት ከሚያሳድርባቸው ጫናም ባሻገር የነሱም ፍርሀትና አድርባይነት ሚና አለው ባይ ነኝ።

ለምሳሌ፤ እነፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በ1993 ዓ.ም በተከሰሱበት ክስ የተከሰተው ጉዳይ የተወሳሰበና የተደበቀ አይደለም። ፍርድ ቤቱ አቃቤ ህግ በምኑም በምኑም ክስ እያጓተተ የግለሰቦችን ነጻነት የሚያውክ ጉዞ ሲጓዝ አቃቤ ህግ ጉዳዩን በጊዜ እንዲጨርስ ጫና ማሳደርና መገሰጽ አለበት። አለበለዚያ አቃቤ ህግ ያሻውን ጊዜ ወስዶና ተዝናንቶ ስራውን የሚሰራ ከሆነ በፖለቲካዊ ምክንያትና በአድልዎ የሚከሰሱ ሰዎች ህጋዊ ላልሆነ የክስ ሂደትና ውጥንቅጥ ይጋለጣሉ። የዘር ማጥፋት ፈጽማችኋል የተባሉ የቀድሞ መንግስት ባላስልጣናት ፍትህ ከተባለ ፍትህ ለማግኘት አስራ ምናምን አመታት ፈጀባቸው። የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በሚያዚያ ወር 1993 ዓ.ም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የሐሰት "የማወናበጃ" ወሬ በመንዛት ለአመፅ አነሳስተዋል በሚል የከሰሳቸው ፕሮፌሰር መስፍንም ራሳቸውን ነጻ ለማድረግ ሰባት አመት ፈጀባቸው። በሰባት ባስራአራት አመታት የሚለካ ፍትህ ፍትህ አይደለም። በዚህ ወር መጀመሪያ አካባቢ የቀረበ የሪፖረተር ዘገባ ፕ/ር መስፍን ከቀረበባቸው ክስ በነፃ ተሰናበቱ ይላል። መጀመሪያ የትኛው ክስ ነው ብዬ ግር ብሎኝ ነበር። የዛሬ ሰባት ዓመት እኛን ያሰደደው ክስተት መሆኑን ስገነዘብ እጅግ በጣም አልገረመኝም። በዚህ እንኩዋንስ ሰባት አመት በማንኛውም መለኪያ ቢመዘን ሰባት ወርም በማይፈጅና ቅንነትና የፍርድ ቤቱ ሀቀኝነት ቢታከልበት ወዲያውኑ መፈታት በሚችል ጉዳይ

ተከሳሹ ሰባት ዓመት ሙሉ ፍትህ ሳያገኙ መቆየታቸው የፍርድ ቤቶቻችንና የፍትህ ስርአታችንን ሁኔታ የሚጠቁም ነው።

## ደርሰን ካናዳን አንሆንም፡ ቢሆንም ቢሆንም

በዚህ በካናዳ እንደዚህ አይደለም ነገሩ። እኔም የካናዳን ተሞክሮ ሳነሳ ደርሰን እንደካናዳ እንዲያደርገን ሳይሆን፡ ዞሮ ዞሮ ህጎቻችንና ዲሞክራሲያችንን ከምእራቡ አለም ስንቀዳ ለመድረስ የምንጠረው የስልጣኔ ጫፍ እነሱን ስለሆንና ምናልባትም የካናዳ የፍትህ አተያይ ምን ያህል ጥብቅ እንደሆነ ለመጠቆም ነው። በካናዳ ምክንያታዊ በሆነ ግዜ ውስጥ የመዳኘት መብት ህገመንግስታዊ መብት ነው። የካናዳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተደጋጋሚ በወሰናቸው ውሳኔዎች እንደጠቀመው፡ አንድ ክስ ለፍርድ ሳይቀርበ ከስድስት እስከ ስምንት ወራት በላይ ከዘገየ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት እንደተጣሰ ተቆጥሮ ክሱ እንዲወገድ ወይም ወደጎን እንዲደረግ ያዛል። ይሄ ባንድ በኩል ምን ያህል ፍርድ ቤቶች ለዚህ መብት ቦታ እንደሚሰጡ ሲጠቁም፡ በሌላ በኩል ደግሞ አቃቤ ህግ ስራውን ባግባቡ እንዲወጣ ያለበትን ከፍተኛ ጫና ያመለክታል። እንጂ እንደኛ ልቅ አይደለም። አንዳንዴ የኛ አገር ፍርድ ቤቶችና ዳኞች የፍትህ ሚኒስቴር ቅርንጫፎች ይመስሉኛል። ወይንም ስራ አስፈጻሚውን ወይንም አቃቤ ህግን ለማረቅ የተቋቋሙ ሳይሆን፡ አቃቤ ህጉን ለመርዳት የተቋቋሙ አካላት ይመስሉኛል።

አንድ በሲያትል የሚገኝ ኢትዮጵያዊ አሜሪካዊ የህግ ባለሙያ በዚህ ጉዳይ ላይ ስንጫወት የአቃቤ ህግ ስራው እውነትን መፈለግ ነው እንጂ ሰዎችን እንደምንም ተሟሙቶ ማስቀጣት አይደለም። በቂም በቀልና እልህ ተነሳስቶ ጥፋተኝነታቸው ያልተረጋገጠባቸውን ሰዎች እስር ቤት በማጎር አይደለም የአቃቤ ህግ ውጤታማነት የሚለካው። ከተከላካይ ጠበቆች ጋር ተባብሮ በመስራት እውነትን በመፈለግ እንጂ። እኔ የኢትዮጵያ አቃብያነ ህግ እውነትን ለመፈለግ ሳይሆን እንደምንም ተጋፍጠው ሰዎችን ለማስቀጣት ሲጥሩ ብመለከት አይደንቀኝም። ፍርድቤቶች ወይም ዳኞች ግን፡ የሰውን መብትና ነጻነት በማስጠበቅ ፋንታና አቃቤ ህግ ጉዳዮቹን አሳማኝ በሆነ መልኩ እንዲያረጋግጥ ከማስረዳት ፋንታ፡ አቃቤ ህግ የሚለውን ሁሉ እንደ ወረደ ተቀብለው ጥፋተኛነቱ ያልተረጋገጠበትን ወይም ከእስር መልስ በሌላ መልኩ ለምሳሌ በከፍተኛ ዋስ አስገድዶ ከፍርድ ቤት ማቅረብ የሚቻልን ሰው እስር ቤት ሲያጉሩ፡ እርግጥም እነኝህ ሰዎች የቆሙት፡ አቃቤ ህግን ለመርዳት ነው፡ ያሰኛል።

## ከእስር መልስ፡ ከነጻነት ወዲያ

ሰውን ማሰር exception ነው። ሁልጊዜ አይከሰትም። ባለፈው ሰሞን ብዙ አሜሪካኖች ሚስቱን ገድሏል ብለው የሚያምኑትና ነገር ግን አስራ ሁለት ሰዎች በሚገኙበት ጁሪ፡ ነጻ የወጣው ኦ ጄ ሲምፕሰን በመሳሪያ አስገድዶ ንብረት ሊዘርፍ ሲል ተያዘ። ነገር ግን በገንዘብ ዋስ ተለቀቀ እንጂ፡ አገኘንህ ብለው ነጭ ዳኞች የዋስ መብት አልነፈጉትም። በቅንጅት አመራር የደረሰውን ታስታውሳላችሁ። ለወራት በየምርጫው ዘመቻ በየቴሌቪዥኑ ጣቢያና በየሬዲዮ ጣቢያው ሲናገሩ በነበሩት ነገር ነው ታስረው የነበረው። በሰአቱ ከዋስ መብት መንፈግ ጀምሮ በማስረጃ አቅራረብ ሂደት ላይ እንዲሁም በመከላከያ ሂደት ውስጥ፡ ዳኞቹ ከአቃቤ ህግ ጎን ቆመው፡ ሲከራከሩና ተከሳሾቹን ሲሞግቱ ለነበረ፡ እንደውም በፍርድ ወንበር ከመሰየማቸው በፊት ፍትህ ሚኒስቴር ተገናኝተው የተመካከሩ ያስመስልባቸው ነበር። በየትኛውም ዘመናዊና ዲሞክራሲያዊ ሀገር ፍርድ ሂደት ውስጥ አቃቤ ህግ ክሱን ያለአንዳች ምክንያታዊ ጥርጣሬ ማረጋገጥ ሲገባው፡ ወይም ሲጠበቅበት፡ ተከሳሽ ወይም ተከላካይ ጠበቆች ግን የሚጠበቅባቸው፡ ትንሽ ጥርጣሬን ብቻ መፍጠር ነው። ቅንጣት ታህልም ጥርጣሬ ባለበት ሁሉ፡ በተለይም የሰው ልጅ ነጻነትና ህይወት አጣብቂኝ ውስጥ በገባበት ቅጽበት ሁሉ፡ ተከሳሾች በነጻ መለቀቅ አለባቸው። በካናዳ እንደዚያ ነው። በኢትዮጵያ ግን ተገላቢጦሹ ይመስላል እውነቱ።

አሁን ኢትዮጵያ ትመራበታለች የሚባለው የኢህአዴግ ህገ መንግስት በመግቢያው ላይ እንዲህ የሚሉ ወርቃማ ህግጋትን አስቀምጧል። በህጋዊ አገዛዝ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ ለመገንባት በመቁረጥ፡ ይህም የሚሳካው የግለሰቦችና የቡድኖች መሰረታዊ ነጻነትና መብት ሲጠበቅ መሆኑን አምነን፡ (አሁንም ይሄ መሰረታዊ መብትና ነጻነቶች የሚለው ቃል ተደግሟል) ይህንን ህገ መንግስት አጸደቅን ይላል። የካናዳ ህገ መንግስት ራሱ እንደዚህ ያለ ወርቃማ መግቢያ የለውም። በዚህ ብቻ አልተገታም። የካናዳ የነጻነትና መብቶች ቻርተር (ሰነድ) ባካተታቸው ሰላሳ አራት አንቀጾች፡ በካናዳ የሚኖሩትን ማናቸውንም ሰዎች መብት የሚያስጠብቅና ከመጣስ የሚከላከሉ መብቶችን አስቀምጧል። የኢህአዴግ ህገመንግስትም፡ ከዚያ ባልተናነሰ እንዲያውም በሰፋ መልኩ፡ የግለሰቦችን መብትና ነጻነቶች የሚቀበሉና የሚከላከሉ ህግጋትን

አስቀምጧል። ስለዚህ በካናዳ እነዚህ መብቶች ለመከበራቸው፡ በኢትዮጵያ ደግሞ ላለመከበራቸውና ወረቀት ላይ ለመቅረታቸው ምክንያቱ ምንድነው ብለን ስንጠይቅ፡ ልዩነቱ ያለው ነጻና ፍትሀዊ ፍርድቤቶች ወይም የፍርድ ስርአት የመኖሩ ላይ ነው። የካናዳ ፍርድቤቶች፡ እድሜ ልካቸውን፡ የካናዳው የመብትና ነጻነቶች ሰነድ ከወጣም በኋላ ይሁን ከዚያ በፊት፡ የግለሰቦችን መብት ሲከላከሉ፡ መንግስት ወይንም የመንግስት አካላት የግለሰቦችን መብት የሚጥስ ድርጊት ሲፈጽሙ ወይንም ህግ ሲያወጡ፡ የለም አይሆንም እያሉ ከስራ አስፈጻሚውና ህግ አውጪው ጋር እየተፋለሙ ነው እዚህ የረደሱት። ይሄ የሆነው፡ ዳኞች በህግ ነጻነት ስለተሰጣቸው ብቻ ሳይሆን፡ የተሰጣቸውን መብት ለማስጠበቅም ቁርጠኛና ዝግጁ ስለሆኑ ነው።

**እንደመዝጊያ፡ እነደምከረም**

መቼም ለተቀማጭ ሰማይ ቅርብ ነው ብላችሁ አትተርቱብኝም። እንጂ፡ በዳኝነት ሙያ ላይ የተሰማራችሁ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ፡ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ፡ ኢኮኖሚያዊ፡ ማህበራዊም እጣ ፈንታና መጪ እድል መወሰን የምትችሉት እናንተ ናችሁ። ከዚህ ቀደም በጻፍኳቸው ጽሁፎች ላይ፡ እዚህ ውጭ አገር ቁጭ ብዬ ይሄን አድርጉ ይሄን ብትፈጥሩ ማለት እንደማይገባና ያንን ብዬ ብገኝ ግን በቅን ልቡና እንዲታይልኝና፡ እንደየተጨባጩ ሁኔታ እንዲተረጎምልኝ ተማጽኜ ነበር። አሁንም፡ ያ ከግምት ይግባልኝ። በፍርሀት የማይኖርና ነጻ የሆነ፡ ወገናዊ ግን ያልሆነ የፍርድ ስርአት ከመሰረትን፡ ምርጫችን ምርጫ፡ ንግዳችን ንግድ፡ ግንኙነታችን ግንኙነት፡ ፍትሀችን ፍትህ፡ ስልጣኔያችንም ስልጣኔ ይሆናል። ይሄንን ደግሞ ለማድረግ፡ ኢህአዴግ ተሳስቶም ይሁን አውቆ፡ ካወጣው ህገ መንግስት ላይ አስቀምጦታል። በየትኛውም ዓለም ባሉ ዴሞክራሲ አለባቸው በምንላቸውም ፍርድ ቤቶች ሳይቀር እንደተደረገው፡ በተለይም የካናዳ ህገ መንግስታዊ ታሪክ እንደሚያሳየው፡ መንግስት ዘወትርም የራሱን ስልጣን ለማብዛት፡ ህጉም እንደፈለገው እንዲተረጎምለት ለማድረግ ከመጣር ወደኋላ አይልም። በተለይ እንደኢህአዴግ ባለ በጠብመንጃ ስልጣን በያዘና ህገ መንግስትንና ፍርድቤቶችን፡ ፍትህንና ህጋዊ አገዛዝን ከማስፈኛ መሳሪያነት ይልቅ፡ የራሱን ስልጣን ለማራዘሚያና የዓለም መንግስታትን ለማታለያ መሳሪያነት ከሚጠቀም መንግስት፡ ፍርድ ቤቶች በተለይ በፖለቲካዊ ጉዳይ ላይ የምር ነጻ እንዲሆኑ ይፈልጋል ብሎ መመኘት የዋህነት ነው። ስለዚህ ቀሪው እዳ ያለው፡ በማናቸውም መንገድ ፍርድ ቤት ገብተው ከሚሰሩ ዳኞች ላይ ይሆናል ማለት ነው። ደፋር፡ ቆራጥ፡ የሾማቸውን መንገስት ለመሞገት የማይፈሩ ዳኞች ካላፈራንና፡ ነጻ ፍርድ ቤት የማቋቋሙ ሂደት ካልተሳካልን፡ ዲሞክረሲ እንደሸወደን፡ ሰብአዊ መብትም እንደራበን እንኖራለን።

አባኪያ ነኝ፡ ከካናዳ

** (ይሄ ጽሁፍ የተጻፈው ኢትዮጵያ ለሚታተመው እምቢልታ ጋዜጣ ነውና በዚያ ማእቀፍ አንብቡት)